**የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**
**የቤተሰብ ችሎት**
**የቤትውስጥ ግንኙነቶች ቅርንጫፍ**

______________________________
የከሳሽ ስም ያትሙ

ከሳሽ፣ _______ DRB _____________
ከ.

______________________________ ዳኛ:- ____________________
የተከሳሽ ስም ያትሙ

ተከሳሽ

**የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መዳፈር ላይ አቤቱታን ማቅረብ**
**ተከሳሹ ይሄ መጥሪያ ላይ ተስማምቷል?** ☐ አዎ ☐ አይ

እኔ፣ ______________________________ ፣ በዚህ ክስመዝገብ ላይ ☐ ከሳሽ ☐ ተከሳሽ ነኝ።
ስምዎን ያትሙ

1. ይሄ ፍርድ ቤት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ጥሰቶች ላይ የመወሰን ስልጣን አለው።

2. የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በሚከተለው ቀን ተሰጥቶ ነበር ______________________________
ትዕዛዙ የተሰጠበት ቀን

3. የሚከተለው ተከሳሽ ወገን የፍርድ ቤት ትዕዛዙን የሚከተለውን ክፍል ጥሷል:- [የሚመለከተው ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ]

☐ ሕጋዊ የልጅ አሳዳጊነት
☐ አሳዳሪነትና ሞግዚትነት
☐ ጉብኝት
☐ ቀለብ የመስጠት ሁኔታ
☐ በጋብቻ የተገኘ ሀብት ክፍፍል
☐ በጋብቻ የተገኘ ዕዳ ክፍፍል
☐ ሌላ:- ______________________________

4. ተከሳሹ የፍርድ ቤት ትዕዛዙን የጣሰበት መንገድ እንደሚከተለው ነው:-

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

## የእፎይታ ጥያቄ

**የሚከተሉትን እንዲፈርድልኝ ለፍርድ ቤቱ በክብር እጠይቃለሁኝ** [የሚመለከተው ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ]

☐ ፍርድ ቤቱ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ መዳፈር ላይ ያቀረብኩትን አቤቱታ ተመልክቶ ተገቢውን ቅጣት እንዲሰጥልኝ።

☐ ይሄንን የፍርድ ቤት ትዕዛዝ የመዳፈር አቤቱታ በማቀርብበት ሰዓት ፍርድ ቤቱ አቤቱታው እንደደረሰው ማሳወቂያ እንዲሰጠኝ። [በዚህ ክስ መዝገብ ላይ **ፍርድ ቤቱ የመጨረሻውን ውሳኔ ከሰጠ 60 ቀናት ወይም ከዚያ በላይ** ከሆነ በኋላ አቤቱታውን የሚያቀርቡ ከሆነ ይሄ ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ]

☐ ፍርድ ቤቱ ችሎት እንደሚሰማ እና ብያኔ እንደሚሰጥ ማሳሰቢያ (NOHODA) እንዲያወጣልኝ። [በዚህ አቤቱታ የሚሰማበት ቀን ላይ ተከሳሹ ወገን የማይገኝ ከሆነ **ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን በፖሊስ አስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ እንዲሰጥ የሚፈልጉ ከሆነ** ይሄ ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ]

**በተጨማሪም ፍትሃዊ እና ተገቢ ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ያመነባቸውን ማንኛውም ሌሎች እፎይታዎች እንዲፈርድ እጠይቃለሁኝ።**

ይሄ አቤቱታ ላይ ከዳኛ ፊት በቃል እንዲደመጥልኝ ☐ እጠይቃለሁኝ። ☐ አልጠይቅም

በሐሰት ምስክርነት ቃል ሕግ መሰረት ከላይ የተጠቀሰው እውነተኛ እና ትክክለኛ ስለመሆኑ አረጋግጣለሁኝ።

*ይሄ ሰነድ ከዩናይትድ ስቴትስ፣ ፖርቶ ሪኮ፣ ዩናይትድ ስቴትስ ቨርጅን ደሴቶች፣ እና በዩናይትድ ስቴትስ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ግዛቶች ወይም ቦታዎች ውጪ የሚፈረም ከሆነ፣ ከመፈረሙ በፊት ተጨማሪ መስፈርቶች መሟላት አለባቸው።*

*ይመልከቱ Super. Ct. Dom. Rel. R. 2(c)(1)(B).*

______________________________
ስምዎን ይፈርሙ በኤሌክትሮኒክስ ለመፈረም በሁለቱም ጎን ላይ /ልክ እንደዚህ/ አግድም ሰረዞችን ያክሉ።

______________________________
ቀን

______________________________
ስምዎን ያትሙ

______________________________
ስልክ ቁጥር

______________________________
የቤት አድራሻ 1

______________________________
ኢሜይል አድራሻ

______________________________
የቤት አድራሻ 2

☐ ተለዋጭ አድራሻ፡- ወከባ እና ጉዳት ይደርስብኛል ብለው በመፍራት የሌላ ሰው አድራሻ ያስገቡ ከሆነ ሳጥኑ ላይ ምልክት ያድርጉ።

**የፍርድ ቤት ትዕዛዙን የመዳፈር አቤቱታውን የሚደግፉ ነጥቦች እና ባለስልጣናቶች**

ይሄንን ጥያቄ በመደገፍ፣ የሚከተለው እመክራለሁኝ፡-

1. Super. Ct. Dom. Rel. R. 4(a)(1), 7(b)(1)(A), እና 70.

2. D.C. Code §§ 11-944, 15-320, 16-911(a) እና 16-916(d).

3. በዚህ መዝገብ ላይ ያለው ማስረጃ።

4. አባሪ የተደረጉት ሰነድ(ዶች )፣ ያሉ ከሆነ።

   [አባሪ የሚያደርጓቸውን ማንኛውም ሰነዶች ይዘርዝሩ]

# በኮቪድ-19 ወቅት የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ለቀረቡ አቤቱታዎች መጥሪያ መስጠት

## *"መጥሪያ" ምን ማለት ነው?*

***መጥሪያ*** በእርስዎ ክስ መዝገብ ላይ ለተከሳሹ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ማዘዣ ወረቀት መስጠት ማለት ነው። የእርስዎ የቤት ውስጥ ግንኙነቶች ያቀረቡት ክስ ላይ ለማንኛውም አቤቱታዎች፣ መልሶች፣ ወይም ሌሎች የክስ ወረቀቶች ("አቤቱታ") ላይ ተከሳሹ ወይም ተከሳሾቹ እንዲገኙ መጥሪያ መስጠጥ አለብዎ።

የፍርድ ቤት ወረቀቱ የሚነግርዎት:-

- ምን ዓይነት የፍርድ ቤት መጥሪያ ዓይነት እንደሚሰጡ
- ለተከሳሹ መጥሪያውን እንደሰጡ እንዴት ለፍርድ ቤቱ እንደሚያሳውቁ
- ስለ መጥሪያው ተጨማሪ መረጃ እንዴት እንደሚያገኙ

## የተለያዩ የክስ መዝገቦች ላይ መጥሪያ የመስጫ ሕጎች አሉ?

አዎ። የክስ መዝገብዎ **ቢከፈትም** ወይም **ቢዘጋም** መጥሪያ የመስጫ የተለያዩ ሕጎች አሉ።

| ይሄ ከሆነ:- | የክስ መዝገብዎ እንዲህ ሊሆን ይችላል: |
|---|---|
| ፍርድ ቤቱ እስካሁኑ የመጨረሻውን ውሳኔ አልሰጠም | ክፍት ነው |
| ፍርድ ቤቱ የመጨረሻውን ውሳኔውን **ከ 60 ቀናት በፊት ሰጥቷል** | ክፍት ነው |
| ፍርድ ቤቱ የመጨረሻውን ውሳኔውን **ከ 60 ቀናት በላይ ሰጥቷል** | ዝግ ነው |

**የክስ መዝገብዎ ክፍት እንደሆነ ወይም እንደተዘጋ እርግጠኛ አይደሉም?** የቤተሰብ ፍርድ ቤት የራስ-እገዛ ማዕከልን በ **202-879-0096** ላይ ደውለው ያግኙ።

## የክስ መዝገቤ <u>ክፍት</u> ነው። ለአንድ ሰው እንዴት የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት እችላለሁኝ?

የክስ መዝገብዎ **ክፍት** ነው፣ የቤት ውስጥ ግንኙነቶችን ሕጎችን [ሕግ 5](#)ን መከተል አለብዎ። ሕግ 5 በሚከተሉት አንዱ መንገድ መጥሪያውን መስጠት ይችላሉ ማለት ነው:-

ለተከሳሹ መጥሪያውን **በእጅ መስጠት**

የተከሳሹ ቤት ውስጥ **አብሮ ለሚኖር ሰው** እና ዕድሜው ከ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ሰው መጥሪያውን መስጠት

የተከሳሹ **ጠበቃ ቢሮ** ውስጥ መጥሪያውን መስጠት

የተከሳሹ (ወይም የተከሳሹ ጠበቃ) የሚታወቅ አድራሻ ላይ **በመጀመሪያ-ደረጃ ደብዳቤ** መጥሪያውን መላክ

በፍርድ ቤቱ ኤልክትሮኒክስ መላኪያ በኩል፣ **ኬዝፋይልኤክስፕረስ**

በሌላ ማንኛውም መንገድ፣ ተከሳሹ በጽሁፍ **እስከተስማማ** ድረስ

***ተከሳሹ ጠበቃ ያለው ከሆነ፣ ለጠበቃቸው መጥሪያ መስጠት አለብዎ።***

## የእኔ <u>ክፍት</u> መዝገብ ላይ መጥሪያዎቹን ሰጥቼአለሁኝ። አሁን ምን ማድረግ አለብኝ?

ለተከሳሹ መጥሪያውን ከሰጡ በኋላ፣ ሁለት ቅደም ተከተሎችን በመከተል ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ አለብዎ:-

1. **የሕግ 5 የመጥሪያ መስጫ ማረጋገጫ ቅጽ ይሙሉ።** ይሄንን ቅጽ እዚህ ላይ ያገኛሉ
2. **ከፍርድ ቤቱ ጋር ቅጹን ይሙሉ።** በኮቪድ-19 የሕዝብ ድንገተኛ ወረርሽኝ ወቅት፣ ቅጹን በሚከተለው አድራሻ በኢሜይል መላክ ይችላሉ FamilyCourtCIC@dcsc.gov.

## የክስ መዝገቤ <u>ዝግ</u> ነው። ለአንድ ሰው እንዴት የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት እችላለሁኝ?

የክስ መዝገብዎ **የተዘጋ** ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ለተከሳሹ ወይም ለተከሳሾቹ የሚሰጡት መጥሪያ **ማዘዣ** ይሰጦታል። የቤት ውስጥ ግንኙነቶችን ሕጎችን ሕግ 4ን መከተል አለብዎ። ሕግ 4 የሚለው **ሁለቱንም መጥሪያውን** እና **አቤቱታዎን** በሚከተሉት አንዱ መንገድ መስጠት አለብዎ:-

ለተከሳሹ የፍርድ ቤት ወረቀቶቹን **እንዲሰጥልዎ** ለአንድ ሰው (18 ዕድሜ ወይም ከዚያ በላይ) ይጠይቁ (*ይሄንን በራስዎ ማድረግ አይችሉም*)

አንድ ሰው (ዕድሜው 18 እና ከዚያ በላይ የሆነ ) የፍርድ ቤቱ ወረቀቶቹን የተከሳሹ ቤት ውስጥ **አብሮ ለሚኖር ሰው** እና ዕድሜው ከ 18 ዓመት በላይ ለሆነ ሰው መጥሪያውን እንዲሰጥ ይጠይቁ(*ይሄንን በራስዎ ማድረግ አይችሉም*)

የተከሳሹ የመጨረሻው የሚታወቅ አድራሻው ላይ ሰነዶቹን **በተረጋገጠ ወይም በተመዘገብ የአደራ ደብዳቤ** በኩል ይላኩ

በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ወቅት፣ እነዚህን ሰነዶች በ **ኢሜይል** ወይም **በጽሁፍ መልዕክት** መላክ ይችላሉ

የእነዚህ መመሪያዎች ተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያዎችን በ እዚህ አገናኝ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

## የእኔ አዲስ ወይም <u>የተዘጋ</u> መዝገብ ላይ መጥሪያዎቹን ሰጥቼአለሁኝ። አሁን ምን ማድረግ አለብኝ?

ለተከሳሹ መጥሪያውን ከሰጡ በኋላ፣ ሁለት ቅደም ተከተሎችን በመከተል ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ አለብዎ:-

1. **የሕግ 4 ስለማድረስ የሚሰጥ ቃለ መሃላ ቅጽ ይሙሉ።** ቃለ መሃላው የፍርድ ቤት ወረቀቶቹን እንደሰጡበት **መንገድ** ይለያያሉ።
   ሀ. ለተከሳሹ በ **ጽሁፍ መልዕክት ወይም በኢሜይል** የሰጡ ከሆነ፣ የሚከተለውን ቃለ መሃላ እዚህ ላይ ይጠቀሙ።
   ለ. ለተከሳሹ በ **ተረጋገጠ የአደራ ደብዳቤ** የሰጡ ከሆነ፣ የሚከተለውን ቃለ መሃላ እዚህ ላይ ይጠቀሙ።
   ሐ. ለተከሳሹ ወይም ከተከሳሹ አብሮ ለሚኖረው ሰው አንድ ሰው ሰነዶቹን **የሰጠ** ከሆነ፣ ይሄንን ቃለ መሃላ እዚህ ላይ ይጠቀሙ።
2. **ለፍርድ ቤቱ ቃለ መሃላውን ይስጡ።** በኮቪድ-19 የሕዝብ ድንገተኛ ወረርሽኝ ወቅት፣ ቃለ መሃላውን በሚከተለው አድራሻ በኢሜይል መላክ ይችላሉ FamilyCourtCIC@dcsc.gov.

## የፍርድ ቤት ሰነዶቹን ለተከሳሽ መስጠት ላይ እገዛ ስፈልግ እንዴት ማግኘት እችላለሁኝ?

እገዛ የሚሹ ከሆነ፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት የራስ-እገዛ ማዕከልን በ **202-879-0096** ላይ ደውለው ያግኙ። የቤተሰብ ፍርድ ቤት የራስ-እገዛ ማዕከል ሂደቱን ያስረዳዎታል፣ እና ተገቢ የሆኑትን የሕግ ወረቀቶች እንዲሞሉ ያግዙታል፣ እና ሌሎች ነፃ የሕግ አማካሪዎች ጋር ይጠቁሞታል።

ነፃ የሕግ እገዛ ሰጪ ድርጅቶችን እንዴት እንደሚያገኙ ጨምሮ፣ ለተጨማሪ መረጃ www.lawhelp.org/dcይጎብኙ፣ ወይም ስለ ጉዳዩ የተቀዱ መልዕክቶችን ለማዳመጥ የዲሲ ባር የሕግ መረጃ እገዛ መስመርን በ 202-626-3499 ደውለው ያግኙ።